በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ
PHARMACEUTICALS FUND AND SUPPLY AGENCY

# የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የአቅም ግንባታ እና የአሰራር ማሻሻያ ጥናት መመሪያ

## 373/2013

ነሐሴ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ማውጫ ....................................................................................................1

መግቢያ....................................................................................................2

የመመሪያው አላማ....................................................................................................3

ክፍል አንድ፡ ጠቅላላ....................................................................................................3

አጭር ርዕስ....................................................................................................3

ትርጓሜ....................................................................................................3

የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን....................................................................................................5

መርሆች....................................................................................................5

ክፍል ሁለት፡ የስልጠና ዝግጅት....................................................................................................6

በመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ዙሪያ የአጭር ጊዜ ስልጠና ማዘጋጀት.................................6

የረጅም ጊዜ እና የውጭ ስልጠናዎች....................................................................................................7

የስራ ላይ ስልጠና መስጠት(on the Job training) ....................................................................................................7

የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት(workshops) ....................................................................................................8

ክፍል ሶስት፡ ድጋፋዊ ክትትል እና ሜንተሪን....................................................................................................9
(Supportive supervisión and mentoring)

ድጋፋዊ ክትትል....................................................................................................9

ሜንተሪንግ....................................................................................................10

ክፍል አራት፡የስልጠና ማቴሪያሎችን ማዘጋጀት....................................................................................................11

ክፍል አምስት፡የተለያዩ ሰነዶችን ማዘጋጀት....................................................................................................12

ክፍል ስድስት፡ የአሰራር ማሻሻያ ጥናቶችን ማከናወን....................................................................................................13
(Operational research on supply Chain management)

ክፍል ሰባት፡ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ....................................................................................................16

ክፍል ዘጠኝ፡ልዩ ልዩ ጉዳዮች....................................................................................................17

መመሪያውን ስለማሻሻል....................................................................................................17

መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ....................................................................................................17

አባሪዎች....................................................................................................18-24

# የአቅም ግንባታ እና የአሰራር ማሻሻያ ጥናት መመሪያ

የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ በአዋጅ ቁጥር 553/99 በተቋቋመውና በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 12(2) የኤጅሲው ስራ አመራር ቦርድ የአፈጻጸም መመሪያዎችን ለማጽደቅ በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህ የአቅም ግንባታ እና የአሰራር ማሻሻያ ጥናት መመሪያ እንዲወጣ ተደርጓል፡፡

## 1. መግቢያ

የመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ስርዓቱን ለማሻሻል ጥናትን መሰረት ባደረገ መልኩ የባለሙያዎችን እውቀትና ክህሎት በተለያዩ የአቅም ግንባታ ስልቶች (ስልጠናዎች፣ ድጋፋዊ ክትትሎች እና ሜንተሪንግ) ማጠናከር አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም በየደረጃው የመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደሩ የሚገኝበትን ደረጃ በተከታታይነት በማጥናት አስፈላጊው የማስተካከያ እርምጃ በወቅቱ ይወሰዳል፡፡

የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የተጣለበትን ሀገራዊ ሃላፊነት ለመወጣት የራሱን ሰራተኞች አቅም ያጎለብታል፣ በአቅርቦት አስተዳዳር ስርዓቱ በየደረጃው ለሚሰሩ ባለሙያዎችንም አቅም ለመገንባት ስልጠናዎችን ይሰጣል፤ የድጋፋዊ ክትትል እና ሜንተሪንግ ስራዎችን ይሰራል እንዲሁም በመድኃኒት አቅርቦት ስርዓቱን ለማሻሻል የሚያግዙ የአሰራር ማሻሻያ ጥናቶችን ያከናውናል፡፡

የአቅም ግንባታ እና የአሰራር ማሻሻያ የስራ ሂደትም ኤጀንሲዉ በዚህ ረገድ የሚያከናዉናቸዉን ተግባራት በተጠናከረ መልኩ ማከናወን ይጠበቅበታል፡፡ኤጀንሲው የሚያከናውናቸው የአቅም ግንባታ እና የአሰራር ማሻሻያ ጥናቶች ሁሉንም የኤጀንሲውን ዋና እና ደጋፊ የስራ ሂደቶች እና በመንግስት መዋቅር በሁሉም ደረጃ በመድሃኒት፣ ህክምና መገልገያዎችና መሳሪያዎች እንዲሁም የላቦራቶሪ ኬሚካሎችንና ሪኤጀንቶችን በማስተዳደር ዙሪያ የሚሰሩ ተቋማትን እና ባለሙያዎችን ማእከል ያደረጉ ይሆናሉ፡፡

ስለሆነም የአቅም ግንባታ እና የአሰራር ማሻሻያ ጥናት ስራዎችን ወጥነትና ግልጽነት ባለዉ መልኩ ለማከናወን እንዲቻል እንዲሁም እነዚህ ስራዎች የሚሰሩበትን አግባብ ለኤጀንሲው ሰራተኞች እና ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ግልጽ ለማድረግ ይህ የአሠራር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency
Office of Board of Directors

## 2. የመመሪያው አላማ

- ለመድሃኒት አቅርቦት አስተዳደሩ ግብዓት የሚሆን ብቁ የሰው ሃይል በየደረጃው እንዲኖር ለማድረግ፣
- የአሰራር ክፍተቶችን በመለየት እና አዳዲስ አሰራሮችን በመተግበር የመድሃኒት አቅርቦት አስተዳደር ስርዓቱ በየጊዜው እየተሻሻለ እንዲቀጥል ለማድረግ ነው።

# ክፍል አንድ

# ጠቅላላ

## 3.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦት አስተዳደር ስርዓት የአቅም ግንባታ እና የአሰራር ማሻሻያ ጥናት መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።
**373/2013**

## 4. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ:-

1. "መድኃኒት" ማለት በሽታን ለመመርመር፣ ለመከላከል፣ ለማስታገስ ወይም ለማከም የሚያገለግል ማንኛዉም ንጥረ ነገር ወይም የንጥረ ነገሮች ዉህድ ማለት ሲሆን በዚህ መመሪያ ዉስጥ "መድኃኒት" ተብሎ የተጠቀሰዉ ቃል የህክምና መገልገያዎችን፣ መሳሪያዎችን እና ኬሚካሎችንና ሪኤጀንቶችንም ይጨምራል።በዚህ መመሪያ ላይ " መድኃኒት" ተብሎ የተጠቀሰው የሕክምና መገልገያዎች፣ መሳሪያዎችን እና ኬሚካሎችንና ሪኤጀንቶችን ይጨምራል።
2. "የመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ስርዓት" ማለት የመድኃኒቶችን መረጣ፣ የፍላጎት ትንበያ እና ምጠና፣ ግዥ፣ ክምችት፣ የክምችት አስተዳደር፣ ስርጭት፣ የአቅርቦት መረጃ አስተዳደር፣ የሰዉ ሃብትና ፈንድ አስተዳደር እና ሌሎች ተያያዥ ስራዎችን ያካትታል።

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ
FDRE Pharmaceuticals Fund And Supply Agency
የቦርድ ጽ/ቤት
Office of Board of Directors

3. “አቅም ግንባታ” ማለት በመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ዙሪያ በኤጀንሲው፣ በጤና ተቋማት እና በጤናዉ ሴክተር በተላያዩ ደረጃዎች ለሚሰሩ የሚመለከታቸው ባለሙያዎች የሚሰጡ ልዩ ልዩ የስልጠና፣ የድጋፋዊ ክትትል እና ሜንተሪንግ ስራዎችን የሚያካትት ሲሆን የአቅም ግንባታ ስራው ከመድሃኒት አቅርቦት አስተዳደር ጋር ግንኙነት ያላቸውን (የሰው ሃይልና ጠቅላላ አገልግሎት፣ ፈንድ አስተዳደር፣ መረጃ አስተዳደር እና የመሳሰሉትን ጨምሮ) በየደረጃው ያሉ ሃላፊዎችን እና ባለሙያዎችን ያካትታል፡፡

4. “ስልጠና” ማለት በመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ዙሪያ የተለዩ የአሠራር ክፍተቶችን ለመሙላት በአቅርቦት ሰንሰለቱ በየደረጃው ለሚሰሩ ባለሙያዎች በማሰልጠኛ ማዕከል ዉስጥ ገጽ ለገጽ ወይም በስራ ላይ የሚሰጥ የአቅም ግንባታ ክንዋኔ ነው፡፡

5. "ድጋፋዊ ክትትል" ማለት በመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ዙሪያ የመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦት ሰንሰለቱን ለማጠናከር በአቅርቦት ስርዓቱ በተለያዩ ደረጃዎች በአካል በመገኘት ያሉትን የአሠራር ክፍተቶች በመለየት የመፍትሔ አቅጣጫዎችን በማስቀመጥ ተግባራዊ መሆናቸዉን ለመከታተል የሚያስችል አሠራር ነው፡፡

6. "ሜንተሪንግ" ማለት በመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦት አስተዳደር ዙሪያ በየደረጃው የሚሰሩ ባለሙያዎች የሚፈለገውን እውቀትና ክህሎት እንዲያዳብሩ ባለሙያው በስራ ገበታው ላይ እያለ በመስኩ የካበተ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች አንድ ለአንድ የሚደረግ የማብቃት ስራ ነው፡፡

7. "የምክክር መድረክ" ማለት በመድሃነት አቅርቦት አስተዳር ዙሪያ የሚያጋጥሙ ችግርችን ከሚለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በጋራ ተወያይቶ ለመፍታት የሚደረግ ስብሰባ ነው፡፡

8. "የስልጠና ማቴሪያል" ማለት ኤጀንሲው በመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ዙሪያ ለሚሰጣቸው የተለያዩ ስልጠናዎች የሚያስፈልጉ የስልጠና ተሳታፊዎች ማኑዋል፣ የአሰልጣኝ መመሪያዎችንና ሌሎች ተያያዥ ማቴሪያሎችን ያካትታል፡፡

9. "ሰነድ" ማለት ከስልጠና ውጭ የሆኑ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ማኑዋሎችን፣ የተለያዩ የአሰራር መመሪያዎችን፣ የአቅም ግንባታ ተግባራት ሪፖርቶችን፣ የጥናት ፕሮፖዛሎችንና ሪፖርቶችን እንዲሁም የድጋፋዊ ክትትል እና ሜንተሪንግ ማቴሪያሎችን ያካትታል፡፡

10."የአሰራር ማሻሻያ ጥናት" ማለት በመድኃኒትና የህክምና መገልገያዎች አቅርቦት ሰንሰለቱ በተለያዩ ደረጃዎች ያለውን የመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ ያሉትን የአሰራር ክፍተቶች በጥናት በመለየትና በመተንተን የመፍትሄ አቅጣጫዎችን ማመላከት ማለት ነው፡፡

11."ማዕከል" ማለት የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ዋናው መስሪያ ቤት ማለት ነው፡፡

12."ቅርንጫፍ" ማለት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ የመድኃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች ማለት ነው፡፡

13."ጤና ተቋማት" ማለት ለህበረተሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ የመንግስት ሆስፒታሎችና ጤና ጣቢያዎች ናቸው፡፡

14."የረዥም ጊዜ ስልጠና" ማለት ለሶስት ወርና ከዚያ በላይ የሚሰጡ ስልጠናዎች ማለት ነው፡፡

15."ኤጀንሲ" ማለት የመድሃት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ ነው፡፡

## 5. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአጀንሲው ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 6. መርሆዎች

የአቅም ግንባታ እና የስራ ላይ ማሻሻያ ጥናት ተግባራት በሚያከናዉኑበት ወቅት የሚከተሉት መርሆዎች ተግባራዊ ይሆናሉ፡፡

1. ጥራትና ተደራሽነት
2. ፍትሃዊነት
3. ግልፅነት
4. ዉጤታማነትና በጋራ መስራት
5. አሳታፊነትና በተግባር የተደገፈ
6. ሃብትን በአግባቡ መጠቀም

# ክፍል ሁለት

## ስልጠና ማዘጋጀት

### 7. በመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ዙሪያ የአጭር ጊዜ ስልጠና መስጠት

1. በመድኃኒት አቅርቦት አስተ-ዳደር ዙሪያ ያሉ የአሠራር ክፍተቶችን በጥናት እንዲለዩ ይደረጋል፤
2. ከተለዩት የአሠራር ክፍተቶች በመነሳት በስልጠናና በምክክር መድረኮች ሊፈቱ የሚችሉትን የመለየት ስራ ይሰራል፡፡
3. የተለዩትን የአሠራር ክፍተቶች ለመሙላት የሚያስችሉ የስልጠና መስኮችን በመለየት እንደየአስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል ይቀመጣሉ
4. በቅደም ተከተላቸው መሠረት ለእያንዳንዱ ስልጠና የስልጠናዉን ዓይነት፣ ይዘትና አላማ፤ስልጠናዉ በስንት ዙር እንደሚሰጥ፣የስልጠናዉን መረሀ-ግብር፣ ስልጠናው የሚሰጥበትንቦታ፣ የሰልጣኞችና የአሰልጣኞች ብዛትና አይነት እና ለስልጠናዉ የሚያስፈልገዉን የገንዘብመጠን ያካተተ ፕሮፖዛል በማዘጋጀት ለበላይ ሃላፊ ይቀርባሉ፤
5. የስልጠናውን ወጭ ለመሸፈን ከተለያዩ ምንጮች ፈንድ ይፈለጋል፤
6. ለስልጠናው የሚያስፈልጉ ማቴሪያሎችንና ቁሳቁሶችን ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር ያዘጋጃል፣ ይከልሳል፤ ለስልጠናዉ ዝግጁ ይደረጋል፡
7. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ሰልጣኞችን እና አሰልጣኞችን በመምረጥ ስልጠናው እንዲሰጥ ይደረጋል፤
8. ለተከናወኑ ስልጠናዎች አባሪ በተደረገዉ ቅፅ መሰረት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን በመያዝ (አባሪ 1) እና ሪፖርት በማዘጋጀት (አባሪ 2) ለሃላፊዎችና ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይላካል፤ ሪፖርቱንም በሃርድ እና ሶፍት ኮፒ በአግባቡ እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡

9. የተሰጡ ስልጠናዎች ስራ ላይ መዋላቸውን የክትትልና ድጋፍ ትግባራት ይከናወናሉ፤

10. የሚሰጡት የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ጥራት እንዲኖራቸዉ ከኤጀንሲዉ የሚመለመሉ አሰልጣኞች በቂ እዉቀትና ክህሎት እንዲኖራቸዉ አስፈላጊ የሆነ የሀገር ዉስጥና የዉጭ አገር ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ኤጀንሲዉ የማሰልጠን ልምድ ያላቸዉን ባለሙያዎች ከሌሎች መንግስታዊ ተቋማትና አጋር ድርጅቶች በአሰልጣኝነት ሊጋበዙ ይችላል።

## 8. የረጅም ጊዜ እና የውጭ ስልጠናዎች

የረጅም ጊዜ እና የዉጭ ስልጠናዎች ተሳትፎ በመንግስት መመሪያ መሰረት የሚከናወን ይሆናል።

## 9. የስራ ላይ ስልጠና መስጠት (on the Job training)

1.. የስራ ላይ ስልጠና የሚሰጥባቸውን ርዕሰ ጉዳዮች እና ስልጠናዉ የሚያስፈልጋቸውን አካላት ይለያሉ፤

2. በተለዩት የስልጠና ርዕሰ ጉዳዮች ዉስጥ ሊዳሰሱ የሚገባቸውን ዝርዝር ጉዳዮች ይለያሉ፤ በዚሁ መሠረት ዝርዝር ይዘቱን (የስልጠና ካሪኩለም)ና የስልጠና ማቴሪያሎችን ዝግጅት ይከናወናል፡

3. የስራ ላይ ስልጠናውን የሚሰጡ በመስኩ ልምድ ያላቸው ባለሙያዎችን በማሳተፍ የተግባር ላይ ስልጠናው ለተለዩት የሚመለከታቸው አካላት እንዲሰጥ ይደረጋል።

4. የስልጠና ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ይቀርባል፤ ተገቢ የሆኑ መረጃዎችም በአግባቡ እንዲያዙና እንዲደራጁ ይደረጋል፤

5.የስልጠናዉ ሂደትና ዉጤት በመገምገም የማስተካከያ ስራዎች ይከናወናሉ።

የኢፌዲሪ የመድሃኒት ፈንድ FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Office of Board of Directors

## 10. የምክክር መድረኮችን ማዘጋጀት (consultative workshops)

1. የምክክር መድረክ የሚያስፈልጋቸውን ርዕሰ ጉዳዮች ከሚመለከታቸው የስራ ሂደቶች ጋር በመሆን የመለየት ስራዎች ይሰራሉ፡፡
2. በምክክር መድረኩ ላይ የሚሳተፉ ባለድርሻ አካላትን በመለየት የምክክር መድረኩ ይዘጋጃል፤
3. የስልጠና ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፤ ተገቢ የሆኑ መረጃዎችንም እንዲያዙ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ድጋፋዊ ክትትል እና ሜንተሪንግ

## (Supportive supervisión and mentoring)

### 11. ድጋፋዊ ክትትል ስለማከናወን

1. በማዕከል ደረጃ አንድ ወጥ የሆነና በየደረጃዉ የሚያገለግል የተቀናጀ የድጋፋዊ ክትትል መመሪያና ቼክሊስቶች ይዘጋጃሉ፡፡

2. በአቅርቦት ሰንሰለቱ ዙሪያ ድጋፋዊ ክትትል የሚደረግባቸዉን መስኮች እንዲለዩ ይደረጋል፤

3.ድጋፋዊ ክትትሉን በተመለከተ ፕሮፖዛል (ድጋፋዊ ክትትሉ የሚካሄድባቸውን ተቋማት፣የሚካሄድበትን ጊዜ፣ የቡድን ስብጥር እና የሚያስፈልጉ የገንዘብና ሌሎች ግብዓቶችን) እቅድ በማዘጋጀት፤ ለቅርንጫፎች እና ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

4. በእቅዱ መሰረት አስፈላጊ ግብአቶችን በማሟላት ድጋፋዊ ክትትሉ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ ነገር ግን ቅርንጫፎች በራሳቸው አቅድ መሰረት ድጋፋዊ ክትትል ሊያከናውኑ ይችላሉ፡፡

5. በማእከል የሚከናወነዉ ድጋፋዊ ክትትል የፌደራል ሆስፒታሎችን፣ የኤጀንሲው ቅርንጫፎችን እና የተመረጡ ጤና ተቋማትን የሚያካትት ሲሆን ቅርንጫፎች ደግሞ በስራቸው የሚገኙ ጤና ተቋማት ላይ ድጋፋዊ ክትትል ያከናዉናሉ፡፡

6. ድጋፋዊ ክትትሉ የተደረገላቸዉ ተቋማት ሃላፊዎች እና የሚመለከታቸዉ ባለሙያዎች ባሉበት በድጋፋዊ ክትትሉ ወቅት የታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ቀርበዉ ዉይይት እንዲደካሄድ ያደርጋል፤ በቀጣይ መሻሻል በሚገባቸዉ ጉዳዮች ላይም መግባባት ላይ በመድረስ የድርጊት መረሀ ግብር ተነድፎ ሁሉም በትግበራ ሂደት የሚመለከተዉን የስራ ድርሻ እንዲወስዱ ያደረጋል፡፡

7. ድጋፋዊ ክትትሉን በተመለከተ በተያያዘው ቅፅ መሰረት(አባሪ-5) ሪፖርት በማዘጋጀት ለሃላፊዎችና ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይቀርባል፣ አስፈላጊውን መረጃም ይያዛል፤

8. በአቅርቦት ስርዓቱ ዙሪያ ምርጥ ተሞክሮ ያላቸዉን ጤና ተቋማትን በመለየት ያከናወኑት ምርጥ ተሞክሮ ተቀምሮ ልምዳቸዉን ለሌሎች ተቋማት እንዲያካፍሉ ይደረጋል፡፡

## 12. ሜንተሪንግ

የመድኃኒት አስተዳደር ስርዓቱን ለማጠናከር በጤና ተቋማት በአካል በመገኘት በጥናት በተለዩ በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በየደረጃው ለሚገኙ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ሜንተሪንግ ይሰጣል። ይህም ስራ በተዘጋጀው “የመድሃኒት አቅርቦት አስተዳደር ሜንተሪንግ ማኑዋል” መሰረት የሚከናወን ይሆናል።

## ክፍል አራት

### 13. የስልጠና ማቴሪያሎች አዘገጃጀት

1. በመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ስርዓት ዙሪያ በባለሙያዎች ዘንድ ያለውን የእውቀትና ክህሎት ክፍተት በማጥናት በአጭር ጊዜ ስልጠና ሊሟሉ የሚችሉትን የመለየት ስራ ይሰራል፡፡

2 ለተለዩት የስልጠና ዘርፎች የስልጠና ካሪኩለም (ስርዓተ ትምህርት) በማዘጋጀት በካሪኩለሙ መሰረት የስልጠና ማቴሪያሎችን እንዲዘጋጁ ይደረጋል፤

3 የተዘጋጁት ረቂቅ የስልጠና ማቴሪያሎችን አውደ ጥናት በማዘጋጀት በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በአስተያየት እንዲዳብር ይደርጋል፤

4 በአውደ ጥናቱ ላይ የተሰጡ አስተያየቶችን እንደየአግባባቸው በማካተት የስልጠና ማቴሪያሎቹ ተጠናቅቀው በሚፈለገው መጠን እንዲታተሙ፤ ለየሚመለከታቸው አካላት እንዲሰራጩና ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ይደረጋል፡፡

6. በየጊዜው ከአሰልጣኞችና ሰልጣኞች የሚሰጡ አስተያየቶችን እንዲሁም ወቅታዊ ሁኔታዎችን መሰረት  በማድረግ የስልጠና ማቴሪያሎቹን እንደየአስፈላጊነቱ  ሪቫይዝ ይደረጋሉ፡፡

# ክፍል አምስት

## 14. የተለያዩ ሰነዶችን ማዘጋጀት

1.የመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደርን ለማጠናከር የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ሰነዶችን ማለትም የአሰራር መመሪያዎችን፣ የድጋፋዊ ክትትልና ሜንተሪንግ መመሪያዎችን፣ መረጃ መሰብሰቢያ፣ ሪፖርት ማድረጊያና ቼክሊስቶችን እንዲሁም የመረጃ ማሰራጫ ቅፆችን ይዘጋጃሉ እንደአስፈላነቱም በተለያየ ጊዜ የመከለስ ስራ ይከናወናል፤

2. የዳሰሳ ጥናቶችንና የአፈፃፀም ሪፖርቶችን መሰረት በማድረግ የአሰራር ሰነድ የሚያስፈልጋቸዉ ስራዎች/ተግባራት እንዲለዩ ይደረጋል፤

3. የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ለማዘጋጀት የሙያ ስብጥሩን በጠበቀ መልኩ ጊዜያዊ የቴክኒክ ቡድን እንዲቋቋሙ ይደረጋል፤

4. አስፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብ ረቂቅ ሰነዶቹ/መመሪያዎቹ እንዲዘጋጁ ይደረጋል፤ የተዘጋጁትን ሰነዶችና መመሪያዎች በሚመለከታቸዉ ባለድርሻ አካላት አስተያየት እንዲሰጥባቸዉ ይደረጋል፤

5. በባለድርሻ አካላት የተሰጡትን አስተያየቶች በማካተትና በበላይ ኃላፊዎችና የሚመለከታቸው አካላት በማስተቸት የመጨረሻዉን ሰነድ እንዲዘጋጁ ይደረጋል፣ ሰነዶቹም በሚፈለገዉ መጠን እንዲታተሙ፤ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲዉሉ ስለ አጠቃቀማቸው የማስተዋወቅ ስራ ይሰራል፤ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ክፍፍል ከተሠራ በኋላ በሚመለከተው የስራ ሂደት በኩል አመቺ የሆነ የስርጭት አዉታርን በመጠቀም የታተሙ ሰነዶች ለሚመለከታቸዉ ቅርንጫፎችና ተቋማት እንዲደርሱ ይደረጋል፤

## ክፍል ሰድስት

## 15. የአሰራር ማሻሻያ ጥናቶችን ማከናወን

1.በአቅርቦት ሰነሰለቱ የተለያዩ ደረጃዎች ያለውን የመድኃኒት አቅርቦት አስተዳደር ስርዓትን ለማጠናከር በአፈፃፀም የሚስተዋሉ የአሰራር ክፍተቶችን በጥናት በመለየትና በመተንተን የመፍትሄ አቅጣጫዎችን የማመላከት ስራዎች ይሰራሉ፤

2. የኤጀንሲውን የአሰራር ስርዓት ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ ጥናቶችን በማከናወን የመፍትሔ አቅጣጫዎችን የሚያስቀምጥ ቡድን በዋናው መስሪያ ቤት ይደራጃል።

3. የተለያዩ የውስጥና የውጭ የአፈጻጸም ሪፖርቶችን፣ የጥናት ውጤቶችን እና የውስጥና የውጭ ተገልጋዮች ጥቆማዎችን መሰረት በማድረግ በየበጀት አመቱ መከናወን ያለባቸውን የአሰራር ማሻሻያ ጥናቶች ይለያሉ።

4. የተለዩትን የጥናት መስኮች አሰራርን በማሻሻል ረገድ ከሚኖራቸው ፋይዳ አንጻር በቅደም ተከተል በማስቀመጥ በእያንዳንዱ ጥናት አማካኝነት ሊመለሱ የሚገባቸው ጥያቄዎች ይቀመጣሉ።

5. ለተለዩት የጥናት መስኮች ከሚመለከታቸው ባለድሻ አካላት ጋር በመተባበር የጥናት ፕሮፖዛል ይዘጋጃል። የጥናት ፕሮፖዛሉ የሚከተሉትን ዋና ዋና መረጃዎች መያዝ አለበት

ሀ. የጥናቱ ርዕስ

ለ. ማጠቃለያ

ሐ. መግቢያ (ስለሚከናወነው ጥናት አጭር ማብራሪያ፣ በጉዳዩ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች ውጤት አጭር ገለጻ)

መ. የጥናቱ አስፈላጊነት

ሠ. የጥናቱ ዓላማዎች

ሰ. ጥናቱ የሚከናወንበት ቦታ

ሸ. ጥናቱን የሚያካሂደው ቡድን (አካል) ሙያዊ ስብጥርና አቅም

ቀ. ጥናቱ የሚካሄድበት ዘዴ

- ጥናቱ የሚካሄድበት አግባብ (ክሮስ ሴክሽናል፣ ኬዝ ኮንትሮል)
- በጥናቱ የሚካቱ አካላት
- የናሙና አወሳሰድ ሂደት
- ቁልፍ መለኪያዎች
- የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጾች
- የመረጃ መሰብሰቢያ ጊዜና ሂደት
- የመረጃ አመዘጋገብ፣ አያያዝና ጥራት አጠባበቅ
- የመረጃ ትንተና እቅድ
- ጥናቱን ለማከናወን ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ስለማግኘት

በ. የጥናቱን ውጤት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የማሳወቂያ እቅድ

ተ. ለጥናቱ የሚያስፈልገው በጀት ከነመግለጫው

ቸ. ለፕሮፖዛሉ ዝግጅት በማጣቀሻነት ጥቅም ላይ የዋሉ የመረጃ ምንጮች ዝርዝር



የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የመድሃኒት ፈንድና አቅርቦት ኤጀንሲ FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency Office of Board of Directors

6.የጥናት ፕሮፖዛሉን ለሚመለከታቸው ሃላፊዎች በማቅረብ እንዲገመገምና እንዲጸድቅ ይደረጋል፤ እንዳስፈላጊነቱም ጥናቱን ለማከናወን ከሚመለከተው አካል ፈቃድ ሊጠየቅ ይችላል፡፡

7. ለጥናቱ የሚያስፈልገውን ወጭ ከተለያዩ ምንጮች ይሰበሰባል፡፡

8. ለጥናቱ የተገኘውን ፈንድ አስተዳደርና አጠቃቀም ሂደት የሚያሳይ መመሪያ ይዘጋጃል፡፡

9. በጥናቱ ለሚሳተፉ ባለሙያዎች የጥናቱን አላማና አጠቃላይ ሂደት በተመለከተ ስልጠና ይሰጣል፡፡

10. ለጥናቱ የሚያስፈልገውን መረጃ ለመሰብሰብ የተዘጋጁትን ቅጾችና መጠይቆች በመጠቀም የሙከራ ጥናት ይደረጋል፡፡

11. ከሙከራ ጥናቱ የተገኙትን ግብዓቶች በመጠቀም በመረጃ መሰብሰቢያ ቅጾችና መጠይቆች እንዲሁም በጥናቱ ሂደት ላይ አስፈላጊውን ማስተካከያ ይደረጋል፡፡

12. ለጥናቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በማሟላት ጥናቱን ይካሄዳል፡፡

13. የጥናቱ የተሰበሰበውን መረጃ ያጠናቅራል፣ ይተነትናል፣ ክፍተቶችን ይለያል፣ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ይዘጋጃሉ፡፡

14. የጥናት ሪፖርት በማዘጋጀት ለበላይ ሃላፊዎች ከቀረቡ በሁዋላ፤ መረጃውን በአግባቡ እንዲያዝ ይደረጋል፡፡

15. የጥናቱን ውጤት ለሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት በማቅረብ በተለዩት ችግሮች እና በተሰጡት ምክረ-ሃሳቦች ላይ የጋራ መግባባት ላይ እንዲደረስ ይደረጋል፡፡

16. የተሰጡትን ምክረ-ሃሳቦች መሰረት በማድረግ የተለዩትን ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል የድርጊት መርሀ-ግብር በማዘጋጀት ባለድርሻ አካላትን በማስተባበር ወደ ትግበራ ይገባል፡፡

17. በተወሰደው የማሻሻያ እርምጃ የመጣውን ለውጥ ይለካል፤ ለበለጠ መሻሻል ቀጣይነት ባለው መልኩ ይሰራል፡

18. የጥናቱ ውጤቱ እንዲታተምና እንዲሰረጭ ይደረጋል፡፡

## ክፍል ሰባት

## 16.ክትትልና ግምገማ ማካሄድ

1. ክትትልና ግምገማ የሚያስፈልጋቸዉን በስራ ሂደቱ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን ይለያል፤ ተግባራቱን ለመለካት የሚያስችሉ ቁልፍ የአፈጻፀም መለኪያዎችን ያዘጋጃል፣ይከልሳል እንዲሁም መለኪያዎችን በመጠቀም ያለዉን ነባራዊ ሁኔታ ለመረዳት የሚያስችል የመነሻ የዳሰሳ ጥናት ያካሂዳል፡፡

2. በአገር አቀፍ ደረጃ በመድሃኒት አቅርቦት ስርአቱ ዙሪያ የሚከናወኑ የአቅም ግንባታና የአሰራር ማሻሻያ ጥናቶች በየወቅቱ እየተሻሻሉ እንዲሄዱ መለኪያዎችን በማውጣት በታቀደ የጊዜ ሰሌዳ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ ይገባል፡፡

3.ቁልፍ የአፈፃፀም መለኪያዎችን በመጠቀም በትግበራዉ የተገኘዉን ዉጤት ይለካል ፣ የልኬቱን ዉጤት ከመነሻ የዳሰሳ ጥናቱ ጋር በማነፃፀር ይተነትናል፣ያደረጃል፤ ውጤቱን መሰረት ያደረገ ማስተካከያ ያደርጋል እንዲሁም እንዳስፈላጊነቱ ለሚመለከታቸዉ አካላት ማሳወቅና ጥቅም ላይ እንዲዉል ያደርጋል፤ የክትትልና ግምገማ ሂደቱን ተጠናክሮ እንዲቀጥል ያደርገል፤

4. በመድሃኒት አስተዳደር ስርአት ውስጥ በየደረጃው የሚሰጠው ስልጠና ጥራት ትክክለኛነት ፣ውጤታማነት ወዘተ በአፈጻጸም ዝቅ ያሉትን በመለየት ተገቢውን ድጋፍና ምክረ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

5.በተራ ቁጥር 4 የተገለጹ መለኪያዎችን ለማስላት ኤጀንሲው ለሁሉም የስራ ክፍሎች በሚያዘጋጀው ዝርዝር እቅድ መሰረት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

FDRE Pharmaceuticals Fund and Supply Agency
Office of Board of Directors

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ጉዳዮች

### 17. መመሪያውን ስለማሻሻል፡-

ይህን መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 18. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፡-

ይህ መመሪያ በኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ ከጸደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

## አባሪዎች

### አባሪ -1፡ የስልጠና መረጃዎች መመዝገቢያ ቅጽ

| ተ. ቁ | የተሳታፊ ስም | ፆታ | ሙያ | ኃላፊነት | የተቋም ስም | ክልል/ ከተማ አስተዳደር | ዞን | ወረዳ | የስራ ቦታ/ ከተማ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | |

## አባሪ 2. የስልጠና ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ

I. አጠቃላይ መረጃ

የስልጠናው ርዕስ ________________________

ስልጠናው የተካሄባቸው ቀናት ________________________

ስልጠናው የተካሄደበት ቦታ ________________________

ስልጠናወን ያዘጋጀው ተቋም ________________________

የስልጠናው ግብ ________________________

የስልጠናዉ ዓላማዎች________________________
___

________________________

________________________

1. መግቢያ

(ስልጠናዉን ለማዘጋጀት ያስፈለገበትን ምክንያት አጭር ማብራሪያ እዚህ ያስቀምጡ)

2. የስልጠናዉ ይዘትና የማስልጠኛ ስልቶች

(በስልጠናዉ የተዳሰሱ ርዕሰ ጉዳዮች፣ ስልጠናዉን የሰጡት ባለሙያዎች፣ እና ስልጠናዉ የተሰጠባቸው ስልቶች በመግለጽ የስልጠናዉን መርሃ - ግብር አባሪ እዚህ አባሪ ያድርጉ)

3. የስልጠና ተሳታፊዎች

(የስልጠናዉ ተሳታፊዎች በሙያ፣ በክልል፣ በተቋም ዓይነት እና በፆታ በመለየት የተወሰነ መረጃ መጻፍና ዝርዝር መረጃዉን ቀጥሎ በተመለከቱት ሠንጠረዦች ይሙሉ)

3. የስልጠናው ወጪ

ለስልጠናዉ የዋለ አጠቃላይ ወጪ (በብር)________________

የገንዘቡ ምንጭ ________________

I. ያጋጠሙ ችግሮች

*(ስልጠናዉን በማዘጋጀትና በመስጠት ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን በአጭሩ ይግለጹ)*

II. በቀጣይ የሚሰሩ ስራዎች ዕቅድ

*(ከስልጠናው የተገኘውን ዕወቀትና ክህሎት ለመተግበር በቀጣይ የሚሰሩ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች በአጭሩ ይግለጹ)*

አባሪ ፫ የተሳታፊዎች ብዛት በተቋማት ዓይነትና በፆታ

| ክልል/ ከተማ አስተዳደር | የተሳታፊዎች ብዛት በተቋማት ዓይነት | | | | | | | የተሳታፊዎች ብዛት በፆታ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሆስፒታል | ጤና ጣቢያ | ጤና ኬላ | ጤና ቢሮ/ ጤና ጥበቃ | መፈአኤ | አጋር ድርጅቶች | ድምር | ወንድ | ሴት | ድምር |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | | | | |

አባሪ 4፡ የተሳታፊዎች ስርጭት በሙያ ዓይነትና በተቋማት ብዛት

| ክልል/ ከተማ አስተዳዳር | የተሳታፊዎች ብዛት በሙያ ዓይነት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሐኪም | ጤና መኮንን | ነርስ | ፋርማሲስት | ድረጊስት | ሌሎች | ድምር |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| | | | | | | | |
| ድምር | | | | | | | |

## አባሪ-5 ፡ የድጋፋዊ ክትትል ስራዎች ሪፖርት ማድረጊያ ቅጽ

| የቅርንጫፉ ስም:__________ ሩብ አመት __________ ቀን:__________ | |
|---|---|
| የድጋፋዊ ክትትሉ ዓላማ | |
| ድጋፋዊ ክትትል የተደረገላቸው ጤና ተቋማት ብዛትና ዝርሰዝር* | |
| ድጋፋዊ ክትትሉን ያደረገው ቡድን አባላት* | |
| ድጋፋዊ ክትትሉ የተደረገበት ጊዜ | |
| ለድጋፋዊ ክትትሉ የወጣው አጠቃላይ ወጪ | |
| የገንዘቡ ምንጭ | |
| በድጋፋዊ ክትትሉ የተገኙ ግኝቶች | |
| ዋና ዋና ተግዳሮቶች | |

| | |
|---|---|
| ጥሩ ተሞክሮዎች | |
| ድጋፋዊ ክትትሉ የተደረገለት ተቋም ድጋፍ | |
| ግብረ-መልስ እና ቀጣይ ስራዎች | |
| የድጋፋዊ ክትትሉ አጠቃላይ ውጤት | |
| ሪፖርቱን ያዘጋጀው ባለሙያ | ስም ..........................................................<br>ፊርማ .................................................... |
| ሪፖርቱን ያጸደቀው: | ስም ..........................................................<br>ፊርማ .................................................... |